# በኢትዮጵያ የተከሰተው ድርቅ የተፈጥሮ ወይስ የፖሊሲ ችግር

Wednesday, 21 October 2015

•

በይርጋ አበበ



የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ በቡድን ሀያ አገራት ስብሰባ ላይ አንድ ንግግር አቀረቡ "በኢትዮጵያ የግብርና ምርት እያደገ ነው" ሲሉ። ፕሬዚዳንቱ ለንግግራቸውም የአንድን ገበሬ ተሞክሮ በማንሳት ገለጹ። ካለፉት 10 ዓመታት ጀምሮ ደግሞ መንግስታዊ መገናኛ ብዙሃን እና መንግስት ራሱ በአንደበቱ በኢትዮጵያ በየዓመቱ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግበናል ሲል ይናገራል። በተለይ ከአንድ ዓመት በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ "ኢትዮጵያ በምግብ ሰብል ራሷን ችላለች" ሲሉ ተናገሩ።

ከወራት በፊት በመገናኛ ብዙሃን ለሕዝብ በቀረበው መረጃ በኢትዮጵያ በትንሹ ከአራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ህዝብ በላይ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ያስፈልገዋል ብሎ የገለጸ ሲሆን ጥናቱ አያይዞም በተለይ በምዕራብ ሐረርጌ አካባቢ በምግብ ዕጥረት ምክንያት ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ህጻናት ለሞት መዳረጋቸውን ይፋ አድርጎ ነበር። በወቅቱ የዚህን ጥናት ሪፖርት በተመለከተ በመንግስት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በኩል መግለጫ የሰጠው የኢትዮጵያ መንግስት ግን በአገሪቱ የድርቅ ችግርም ሆነ የምግብ እጥረት እንደሌለ አስታወቀ። ባሳለፍነው ሳምንት ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተለያዩ ኤጀንሲዎች፣ ከእርዳታ ሰጭ ተቋማት ተወካዮች እና ከመያዶች ጋር ባደረገው ውይይት በአሁኑ ወቅት 8 ነጥብ 2 ሚሊዮን የአገሪቱ ዜጋ የምግብ እርዳታ ያስፈልገዋል ሲል አስታውቋል። ለዚህም ቀደም ሲል ተይዞ ከነበረው በተጨማሪ ከ 10 ቢሊዮን ብር ያላነሰ ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ገልጿል።

አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝም መንግስታቸው በአሁኑ ወቅት ከካዝናው አውጥቶ በድርቁ ለተጎዱ ዜጎች ከሚያደርገው እርዳታ ላይ ቅድሚያ የሰጠው ለነብሰ ጡር፣ ለሚያጠቡ እናቶች እና ለህጻናት መሆኑን በቅርቡ በመንግስታዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ተናግረዋል። ለመሆኑ ለዚህ የበቃነው በፖሊሲ ምክንያት ወይስ በተፈጥሯዊ ችግር? መንግስት ምን ይላል፣ ምሁራንስ? የሚሉትን ነጥቦች ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን።

## ኤልኒኖ ምንድን ነው መነሻውስ?

የኢትዮጵያ ሚትዎሎጂ ድርጅት ቅድመ መከላከልና ዝግጁነት ዳይሬክተር ዶ/ር ዲሪባ ቆርቻ በነሐሴ ወር ለጋዜጠኞች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ በኤል ኒኖ ምክንያት በተፈጠረ የአየር ንብረት ለውጥ የዝናብ እጥረት ሊከሰት እንደቻለ ተናግረው ነበር። ኤልኒኖ ምንድን ነው? ኤል ኒኖ በመፈጠሩስ ምን ጉዳት ይከሰታል? የሚሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች መልስ እንሰጥባቸዋለን።

ዊኪፔዲያ የተባለው ድረ ገጽ ስለ ኤልኒኖ ከዚህ በታች ያለውን ትርጓሜ ይሰጣል። ኤል ኒኖ የሚለው ቃል የስፔኖች ቋንቋ ሲሆን ትርጓሜውም የፓስፊክ ውቅያኖስ የታችኛው ክፍል ከ **0.5** ድግሪ ሴንቲግሬድ በላይ ሲሞቅ በመሬት ላይ የሚፈጥረው ድርቅ ነው። ኤልኒኖ በተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ ጠብቆ የሚነሳ ሳይሆን መደበኛ ባልሆነ የጊዜ ስሌት **(**አብዛኛውን ጊዜ ከሁለት እስከ ሰባት ዓመታት ውስጥ**)** ነው የሚፈጠረው። የውቅያኖሱ የታችኛው ክፍል አንዴ ከሞቀ ከዘጠኝ ወራት እስከ ሁለት ዓመታት ድረስ እንደሞቀ ሊቆይ ይችላል። በዚህ የተነሳም በበርካታ አገሮች ላይ በግብይት እና በምርት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠር ይችላል። በተለይ በማደግ ላይ ባሉ እና ገና ባላደጉ ኢኮኖሚያቸውን በግብርና **(**እንስሳት እርባታ፣ እርሻ እና አሳ ምርት**)** ላይ የመሰረቱ የፓስፊክ ውቅያኖስ ተጎራባች አገሮች በኤልኒኖ ምክንያት ተጎጂ ይሆናሉ።

## የኢትዮጵያ የድርቅ ታሪክ

ኢትዮጵያ ላለፉት መቶ ዓመታት በየአስር ዓመቱ የጊዜ ልዩነት በድርቅ የምትጠቃ አገር መሆኗ በርካታ የኢኮኖሚ ምሁራን ይናገራሉ። የቅርብ ጊዜያቶቹን ብናነሳ እንኳ በ **1966/67**፣ **1976/7**፣ **1986/7**፣ **1996/7** እና በዚህ ዓመት የተከሰቱትን ማንሳት ይቻላል። በእነዚህ ጊዜያትም በርካታ ዜጎች በርሃብ ምክንያት ለሞት እና ለስደት የተዳረጉ ሲሆን የአገሪቱን ገጽታም በድርቅ ምክንያት እንድትታወቅ ያደረጉ ኩነቶች ናቸው። በተለይ በ **1977** እና በ **1997** ዓ**.**ም የተከሰቱት ድርቆች የፈጠሩት ርሃብ በርካታ ዜጎችን ለሞት የዳረጉ ነበር። በዚህ ዓመት የተከሰተው ድርቅም በተለይ በምስራቃዊ እና ደቡባዊ የኦሮሚያ ክፍል፣ በአፋር ክልል እና በኦጋዴን ግዛቶች ላይ በርካታ ዜጎችን ለሞት መዳረጉን የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድረ ገጾች ዘግበዋል።

## በዘንድሮው ድርቅ ዙሪያ የመንግስት እርምጃ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት አስተያየት



የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን ጨምሮ የተወሰኑ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን እና በአገር ቤት ደግሞ የግል መገናኛ ብዙሃን ተቋማት በኢትዮጵያ ድርቅ መፈጠሩን ይፋ ካደረጉበት ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ አስተያየቶች ተሰምተዋል። የእንግሊዙ ዘጋርዲያን ጋዜጣ በነሃሴ **19** ቀን **2008** ዓ**.**ም ዕትሙ **"**የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ካወጣው የ **4** ነጥብ **5** ሚሊዮን በተጨማሪ **1** ነጥብ **5** ሚሊዮን ዜጎች ተጨምረው በድምሩ ከስድስት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች በዚህ ዓመት መገባደጃ ከ **230** ሚሊዮን ዶላር በላይ የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ኢትዮጵያዊያን የድርቅ ሰለባ ይሆናሉ**"** ብሎ ዘግቦ ነበር። ጋዜጣው በወቅቱ ዜናውን የሰራው **"UN officer for the coordination of Humanitarian Affairs, World food program, UN children's Agencies and Unicef"** የተባሉ ዓለም አቀፍ ተቋማትን ዋቢ በማድረግ ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ምትኩ ካሳ ነሃሴ **6** ቀን **2008** ዓ**.**ም ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ **"**በድርቅ ለተጠቁ አካባቢዎች የምግብ አቅርቦት ስራ መንግስት ሰርቷል። ወደ አካባቢዎቹም **(**ፈንታሌ፣ አሚባራ እና ገዋኔ አካባቢዎች**)** አጓጉዟል። በአካባቢዎቹ የሚገኙ እንስሳትም በምግብ እጥረት እንዳይጎዱ ስራ ተሰርቷል**"** ብለው ተናግረው ነበር። የመንግስት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ**/**ቤት ኃላፊ የነበሩት አቶ ሬድዋን ሁሴንም የተከሰተው ድርቅ ይህን ያህል አሳሳቢ እንዳልሆነ እና መንግስት ለዜጎቹ የሚሆን የምግብ አቅርቦት እንዳለው ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተናግረው ነበር።

## ስለ ድርቁ ምሁራን እና የፖለቲካ ባለሙያዎች ምን አሉ**?**

የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የቀድሞው ሊቀመንበር አቶ ሙሼ ሰሙ ከሰንደቅ ጋዜጣ ጋር በስልክ ባደረጉት ቃለ ምልልስ **"**ድርቅ በኢትዮጵያ ሲፈጠር ይህ የመጀመሪያው አይደለም ባለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ በየአስር ዓመቱ ልዩነት ይፈጠራል**"** ያሉ ሲሆን **"**ነገር ግን ድርቁ በዜጎች ላይ የሚፈጥረው ችግር ምክንያቱ በመንግስት የግብርና ፖሊሲ ችግር የተነሳ ነው**"** ብለዋል። የቀድሞው የፓርላማ አባል እና ኢኮኖሚ ባለሙያው አቶ ተመስገን ዘውዴ በግል የፌስ ቡክ ገፃቸው ላይ **"**በኢትዮጵያ ላለው የኑሮ ውድነትም ሆነ አሁን ለተፈጠረው ድርቅ እና ድርቁን ተከትሎ ለሚከሰተው ርሃብ ተጠያቂው የመንግስት ፖሊሲ ነው**"** ሲሉ ጽፈዋል። **(**መንግስት የተለያዩ የኢኮኖሚ ሰጭ ተቋማትን **(**ንግድ ባንክ አየር መንገድ መድን ድርጅት እና ሌሎች**)** በቁጥጥሩ ስር ማድረጉም ተገቢ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል።**)**

ሁለቱ ግለሰቦች የመንግስትን የግብርና ፖሊሲ ለርሃብ ዳርጎናል ያሉበትን ምክንያት ሲያቀርቡም "መንግስት የሚከተለው በትናንሽ የአርሶ አደር ማሳ ላይ ምርታማነትን አሳድጋለሁ ብሎ መነሳቱ ትክክል አይደለም" ያሉ ሲሆን በአንጻሩ በሰፋፊ እርሻ ላይ መሰረት ያደረገ የግብርና ፖሊሲ ብንከተል አገሪቱ ምርታማነቷ ይጨምራል ብለዋል። አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በቅርቡ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዙሪያ ባወያዩበት ወቅት "የተቃዋሚዎች የግብርና ፖሊሲ አጥፊ ፖሊሲ ነው" ብለው መናገራቸውን በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ዘግበን ነበር። አቶ ኃይለማሪያም መንግስታቸው የያዘው የግብርና ፖሊሲ አዋጭ መሆኑንም አንክሮ ሰጥተው የተናገሩበት ሲሆን ይህን ፖሊሲ መቀየርም ሆነ ማስተካከል የማይታሰብ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ተመስገን ዘውዴ ቀደም ባሉት ሳምንታት ብሎጋቸው ላይ "በኢትዮጵያ ያለው የበጎ አድራጎት ማህበራት አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብት ጥበቃ ህዝብ ማስተማር አይችሉም ይላል። በዚህ ህግ የተነሳም ብዙ ድርጅቶች ኢትዮጵያን ጥለው ወጥተዋል። እነዚህ ድርጅቶች ቢኖሩ ኖሮ አሁን የተከሰተው ድርቅ እና መፍትሔውን ለዓለም ጆሮ ቀድሞ ይደርስ ነበር" ሲሉ ነበር ያሰፈሩት። አያይዘውም አቶ ተመስገን እንዳሰፈሩት "በኢትዮጵያ ያለው መንግስት ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ያልተላበሰ በመሆኑ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ የሚመለከተው በፖለቲካ መነጽር ብቻ ነው። ይህ በመሆኑም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባውን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው ችግሩን መሸፋፈንን ይመርጣል" ሲሉ አስረድተዋል።

በርካታ ዓለም አቀፍ ጫናዎች የበዙበት የኢትዮጵያ መንግስት ሰሞኑን በሰጠው መግለጫ የድርቁ መጠን ከአቅሙ በላይ እንደሆነበት አስታውቋል። ለዚህም ከካዝናው ከሚያወጣው ገንዘብ በተጨማሪ ሌሎች ልማቶችንም በማጠፍ ቢሆን ለድርቁ ተጎጂዎች ትኩረት እንደሚያደርግ ቃል የገባ ሲሆን እርዳታ የሚያደርጉ መንግስታት እና ድርጅቶችም እጃቸውን እንዳይሰበስቡበት ጠይቋል። በአጠቃላይም ከአስር ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብም እንደሚያስፈልገው በቅርቡ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ባደረገው ውይይት ይፋ አድርጓል።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ በቅርቡ ወደ ሶማሊያ ክልል ተጉዘው ከነዋሪዎች ጋር ባደረጉት ውይይት መንግስታቸው በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች አስቸኳይ እርዳታ እንደሚያቀርብ መናገራቸውን የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል።

## ቀጣይ የድርቁ መጠን

ኤልኒኖን ተከትሎ በኢትዮጵያ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር 4 ነጥብ 5 እንደሚሆን በነሐሴ ወር የተካሄደ ጥናት ይፋ አድርጎ የነበረ ቢሆንም በቅርቡ ይፋ በሆነ መረጃ ደግሞ የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ዜጎች ቁጥር ወደ 8 ነጥብ 2 መድረሱ ተገልጿል። የችግሩ ሰለባዎች ግን በዚህ አሃዝ ብቻ የሚገታ እንዳልሆነ አንድ ጥናት አስታውቋል። ጥናቱ እንደሚያትተው በዚህ ዓመት መጨረሻ የተረጂዎች ቁጥር ወደ 15 ሚሊዮን ያሻቅባል ይላል።

የሰንደቅ ምንጮች ከተለያዩ አካባቢዎች ባደረሱን መረጃ ደግሞ የድርቁ መጠን ተባብሶ መቀጠሉን ነው። ምንጮቻችን በኦሮሚያ፣ አፋር እና ደቡብ ክልል የድርቅ መጠኑ መባባሱን የገለጹ ሲሆን ይህም የተጎጂዎቹን ቁጥር ከፍ እንደሚያደርገው ይጠበቃል ብለዋል።

መንግስት የግብርና ፖሊሲዬ ችግር የለበትም፣ የተቃዋሚዎች ፖሊሲም ቢሆን አጥፊ ነው ሲል፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እና ከፖለቲካ ፓርቲም ሆነ ከፖለቲካዊ ተሳትፎ ውጭ የሆኑ ምሁራን ደግሞ የመንግስትን ፖሊሲ ይተቻሉ። መንግስት ለድርቁ እና ድርቁን ተከትሎ ለሚነሱ ምክንያቶች ኤልኒኖን እና ተፈጥሮን ተጠያቂ ያደረገ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ኤልኒኖም ሆነ ተፈጥሯዊ የዝናብ እጥረት እና ድርቅ በአገሪቱ ሲከሰት ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፣ የቆዬ ታሪክ ነው። ነገር ግን መንግስት ፖሊሲውን ሊፈትሽ እና ቅድመ ዝግጅቱንም ሊያጠናቅቅ ይገባ ነበር ሲሉ ይናገራ